www.abyssinialaw.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ—መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 40
ADDIS ABABA–8th April, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፳/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፪ሺ፩፻፳፰

## CONTENTS

Proclamation No. 320/2003
Ethiopian Intellectual Property Office
Establishement Proclamation .................. Page 2128

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፳/፲፱፻፺፭

## የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈጽም ወይም ተፈፃሚነታቸውን የሚከታተል እንዲሁም አስፈላጊውን አቅም በመገንባት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥ መንግሥታዊ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፳/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

፩· "አእምሯዊ ንብረት" ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያለ ሕጋዊ መብት ሲሆን ፓተንትን፣ የንግድ ምልክትን፣ የምስክር ወረቀትንና ኮፒራይትን ይጨምራል።

፪· "ፓተንት" ማለት የፈጠራ ሥራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን በፈጠራ፣ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፫/፲፱፻፹፯ መሠረት በፈጠራ፣ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚሰጠውን የአስገቢ ፓተንት፣ የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን ይጨምራል።

## PROCLAMATION No. 320/2003

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHEMENT OF THE ETHIOPIAN INTELECTUAL PROPERTY OFFICE

WHEREAS, it is found necessary to establish a government body which is responsible to implement or follow up the implementation of national laws governing intellectual property as well as to build the necessary capacity to render efficient and effective services.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short title*

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Intellectual Property Office Establishement Proclamation No. 320/2003."

2. *Definition*

1) "Intellectual property" means a legal right over a creative work of the human intellect and includes patent, trademark, registration certificate and copyright.
2) "Patent" means the title granted to protect inventions and includes patent of introduction, utility model cetificate and industrial design registration certificate granted to inventions, minor inventions and industrial designs in accordance with the Proclamation Concerning Inventions, Minor Inventions and Industrial Designs, Proclamation No. 123/1995

www.abyssinialaw.com

፫· "የንግድ ምልክት" ማለት አንድን ምርት ወይም አገልግሎት ከተመሳሳይ ምርት ወይም አገልግሎት ለመለየት የሚያስችል ምልክት ወይም የምልክቶች ቅንጅት ነው። ምልክቶቹ ፊደላት፣ ቃላት፣ ቁጥሮች፣ ምስሎችና የቀለሞች ቅንጅት ወይም የተዘረዘሩት ምልክቶች ማንኛውም ቅንጅት ሊሆን ይችላል።

፬· "ኮፒ ራይት" ማለት እንደ ሥነ ጽሑፍና ኪነ ጥበብ ባሉ ሥራዎች ላይ ያለ መብት ሲሆን አጎራባች መብትንም ይጨምራል።

፭· "አጎራባች መብት" ማለት ከዋኞች፤ የቀረፀ ድምጽና የኦዲቪዥዋል አሳታሚዎች የብሮድካስቲንግ ኬብል አሰራጪዎች በሥራዎቻቸው ላይ ያላቸው መብት ነው።

፫· *መቋቋም*

፩· የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው መንግሥታዊ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ይሆናል።

፬· ዋናው መሥሪያ ቤት

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ድሬዳዋን ጨምሮ በክልሎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

፭· የጽሕፈት ቤቱ ዓላማዎች

ጽሕፈት ቤቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፣

፩· አእምሯዊ ንብረት በቂ የሕግ ጥበቃ የሚያገኝበትንና በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

፪· በፓተንት ሰነዶች የታቀፉ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ ማሰራጨትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማበረታታት፣

፫· የአእምሯዊ ንብረት ፖሊሲዎችን ህጎችን ማጥናት፣ መተንተንና ለመንግሥት ሃሳብ ማቅረብ፣

፬· በሕዝቡ ዘንድ የአእምሯዊ ንብረት እውቀትና ግንዛቤ እንዲዳብር ማድረግ።

፮· የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩· የፓተንትና የንግድ ምልክት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን በመቀበል አግባብ ባለው ሕግ መሠረት አስፈላጊውን ምርመራ በማካሄድ ወይም እንዲካሄድ በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት፣

፪· በሕጋዊ ሰነድ ጥበቃ የተደረገላቸውን የውጭና የአገር ውስጥ የፈጠራ ሥራዎችን በጥቅም ላይ መዋላቸውን መከታተል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግዴታ ፈቃድ መስጠት፣

፫· የፓተንት ማመልከቻ ከመቅረቡ ወይም ቴክኒካዊ ችግሮችን ለመፍታት ምርምር ከመደረጉ በፊት በመስኩ የተሰሩ ተመሳሳይ የፈጠራ ሥራዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ የፍለጋ መጠይቆችን መቀበል፤ የፍለጋ አገልግሎት መስጠት፤

፬· የንግድ ምልክት ማመልከቻዎች ከመቅረባቸው በፊት ቀደም ሲል ተመሳሳይ ምልክቶች አለመመዝገባቸውን ለማረጋገጥ የፍለጋ መጠይቆችን መቀበል፤ የፍለጋ አገልግሎት መስጠት፤

፭· የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች ማተምና ማሠራጨት፣

3) "Trademark" means any sign or combination of signs capable of distinguishing goods or services from similar goods or services. Such signs include letters, words, numerals, figurative elements and combination of colours or any combination thereof.

4) "Copyright" means a right over a creative work such as literary and artistic works and includes neighboring rights.

5) "Neighboring rights" means the rights of performers, printers of phonograms and producers of audiovisual, and broadcasting and cable distribution organizations over their works.

3. *Establishment*

1) Ethiopian Intellectual Property Office (hereinafter referred to as "the Office") is hereby established as an autonomous government body having its own legal personality.

2) The Office shall be accountable to the Ethiopian Science and Technology Commission.

4. *Head Office*

The Office shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices in Dire Dawa and other regions as may be necessary.

5. *Objectives of the Office*

The Office shall have the following major objectives:

1) to facilitate the provision of adequate legal protection for and exploitation of intellectual property in the country;

2) to collect, organize and disseminate technological information contained in patent documents and encourage its utilization;

3) to study, analyze and recommend policies and legislations on intellectual property to the Government;

4) to promote knowledge and understanding of intellectual property among the general public.

6. *Powers and Duties of the Office*

The Office shall have the following powers and duties:

1) to receive applications for patent and trademark registration certificate and give appropriate decisions after undertaking or causing to be undertaken the necessary examination in accordance with the relevant law;

2) to follow up the exploitation of legally protected foreign and local inventions and issue compulsory licenses when necessary;

3) to receive search requests and render search services to determine the existence of similar inventions prior to an application for a patent is filed or before a research activity to solve a technical problem is undertaken;

4) to receive search requests and render search services to determine the existence of similar registered trademarks before a trademark application is filed;

5) to publish and disseminate Intellectual property rights Gazette;

www.abyssinialaw.com

፮· የአእምሯዊ ንብረት መብቶችን የሚመለከት የመረጃ ሥርዓት መፍጠርና ለተጠቃሚዎች አገልግሎት መስጠት፣
፯· መንግሥት የሚያወጣቸው የአእምሯዊ ንብረት አዋጆችና ደንቦች ሥራ ላይ ማዋል፤
፰· በቅድሚያ የትኩረት መስኮች በፓተንት ሰነዶች የታቀፉ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን መምረጥና ማሰራጨት እንዲሁም ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲውሉ ማበረታታት፤
፱· የፓተንትና የንግድ ምልክት የጥበቃ ጊዜ ማራዘምና የእድሳት ማመልከቻዎችን መቀበል፤ መሰብሰብና ማደራጀት፤ በሕግ መሠረት ውሳኔ መስጠት፤
፲· በሕዝቡ ዘንድ የአእምሯዊ ንብረት ግንዛቤ ለመፍጠርና ለማጠናከር ሰፊና የተቀናጀ የአህዝቦት ስልት መቀየስና ሥራ ላይ ማዋል፤
፲፩· በአእምሯዊ ንብረት ጉዳዮችና ጭብጦች ላይ ጥናቶች ማካሄድ፣ በብሄራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በአእምሯዊ ንብረት መስክ ያሉትን እድገቶች መከታተል፤ የሕግና የፖሊሲ ሃሳቦችን አዘጋጅቶ ለመንግሥት ማቅረብ፤
፲፪· የአእምሯዊ ንብረት ፖሊሲዎችንና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሥራ ላይ ማዋል እና/ወይም ሥራ ላይ መዋላቸውን መከታተል፤
፲፫· በአእምሯዊ ንብረት ጉዳዮች ላይ ለሕዝብ፣ ለመንግሥት፣ ለግል ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት እንዲሁም ለግለ ሰቦች የምክር አገልግሎት መስጠት፤
፲፬· የፈጠራ ሠራተኞች፣ የደራሲያን፣ የሙዚቀኞችና መሰል ማኅበራት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ማኅበ ራቱን መደገፍና ማጠናከር፣
፲፭· የአእምሯዊ ንብረት ባለቤቶችንና የፈጠራ ሥራቸውን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሹ ባለሃብቶችን ለማገናኘት የሚረዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
፲፮· ከሌሎች የውጪ አገር፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የአእ ምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤቶች ጋር ግንኙነትና ትብብር መፍጠር፣
፲፯· ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣
፲፰· የንብረት ባለቤት መሆንና ውል መዋዋል፣
፲፱· በራሱ ስም የመክሰስና መከሰስ፣
፳· ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን።

፯· <u>የጽሕፈት ቤቱ አቋም</u>

ጽሕፈት ቤቱ፤
፩· ብሔራዊ የአእምሯዊ ንብረት ምክር ቤት ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ·
፪· በመንግሥት የሚሾም አንድ ዳይሬክተር ጄኔራል እና
፫· አስፈላጊ ሠራተኞች
ይኖሩታል።

፰· <u>የምክር ቤቱ አባላት</u>

የምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት በመንግሥት ይሰየማሉ።

፱· <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
፩· ለመንግሥት በሚቀርቡ የፖሊሲ ሃሳቦች ላይ ጽሕፈት ቤቱን ማማከር፤
፪· በጽሕፈት ቤቱ ተዘጋጅተው በሚቀርቡ መመሪያዎች፤ ፕሮግራሞች እና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ማማከር፤
፫· በዳይሬክተር ጄኔራሉ በሚቀርቡ የጽሕፈት ቤቱ አስተዳደር እና አመራር በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ማማከር እና
፬· የራሱን የአሠራር ደንብ ማውጣት።

6) to create an information system on intellectual property rights and provide services to users;
7) to impement laws and regulations on intellectual property rights issued by the Government;
8) to select and disseminate technological information contained in patent documents in priority areas and encourage their utilization for economic and social benefits;
9) to receive, organize and decide on applications for extension and renewal of patent and trademark protection in accordance with the law;
10) to design and implement extensive and coordinated popularization strategy to create and strengthen awareness about intellectual property among the general public;
11) to undertake studies on intellectual property matters and issues, follow up national and international developments in the field of intellectual property; develop and submit policy and ligislative proposals to the Government;
12) to implement and/or follow up the implementation of intellectual property, policies as well as International agreements to which Ethiopian is a party.
13) to render advisory services on intellectual property matters to public, state, private organizations and professionals association as well as individuals;
14) to ficilitate the establishement of, support and strengthen inventors, authors and musicians associations as well as similar societies;
15) to facilitate conditions that will help to create linkages between intellectual property owners and enterepreneurs who wish to exploit their creative works;
16) to establish relations and cooperation with foreign nationals, regional and international intellectual property offices;
17) to charge fees for the services it renders;
18) to own property and enter into contract;
19) to sue and be sued in its own name;
20) to undertake such other duties necessary for the implementation of its objectives.

7. *Organization of the Office*

The Office shall have:
1) A National Intellectual Property Council (herein after referred to as "the Council";
2) A Director General to be appointed by the Governement; and
3) The necessary staff.

8. *Members of the Council*

The chairman and members of the Council shall be designated by the Governement.

9. *Powers and duties of the Council*

The Council shall have the powers and Duties to:
1) advise the Office on policy proposals to be submitted to the Government;
2) render advice on guidelines, programs and activity reports prepared by the Office;
3) advice on other matters related to managerial and administrative issues of the Office submitted by the Director General, and
4) draw its own rules of procedures.

www.abyssinialaw.com

፲· የምክር ቤቱ ስብሰባ

፩· ምክር ቤቱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

፪· ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።

፫· ምክር ቤቱ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርበው በተባበረ ድምፅ ይሆናል። የተባበረ ድምፅ ከሌለ በድምፅ ብልጫ የውሳኔ ሃሳብ ይተላለፋል። የድምጽ አሰጣጡ እኩል በእኩል የተከፈለ ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፲፩· የዳይሬክተር ጄኔራል ሥልጣንና ተግባር

፩· ዳይሬክተር ጄኔራሉ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ጽሕፈት ቤቱን የማስተዳደርና ሥራውንም የመምራት ኃላፊነት አለበት።

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዳይሬክተር ጄኔራሉ፣

ሀ) በፌዴራል የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ለ) የጽሕፈት ቤቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶች አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

ሐ) የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣ እንዲሁም የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፣

መ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ጽሕፈት ቤቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል።

፫· ዳይሬክተር ጄኔራሉ ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፲፪· በጀት

፩· የጽሕፈት ቤቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፤

ሀ) ከፌዴራል መንግሥቱ የሚመደብ ድጎማ፣

ለ) ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ እና፣

ሐ) ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ።

፪· ጽሕፈት ቤቱ የሚያገኘውን ገቢ በአገሪቱ የፋይናንስ ሕግና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ያውላል።

፲፫· የሂሳብ መዛግብት

፩· የጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪· የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፲፬· የመተባበር ግዴታ

ማናቸውም ሰው ወይም መንግሥታዊ ወይም የግል ድርጅት ወይም ተቋም ለጽሕፈት ቤቱ ሥራ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

፲፭· ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ህጎች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

10. *Meeting of the Council*

1) The Council shall have a regular meeting once every three months. However, it may at any time hold an extraordinary meeting whenever necessary.
2) There shall be a quorum where more than half of the members of the Council are present in its meeting.
3) Recommendations of the Council shall be passed by consensus. In the absence of consensus, the recommendation shall be passed by a majority vote. In case of a tie, the chairman shall have a casting vote.

11. *Powers and Duties of the Director General*

1) The Director General shall be the chief executive officer of the Office and shall direct and administer the activities of the Office.
2) Without limiting the generalities of Sub-Article (1) of this Article, the Director Genral shall:
   (a) employ and adminster employees of the Office following the basic principles of the Federal Civil Servant Laws;
   (b) prepare the short, medium and long-term plans of the Office and implement same upon approval;
   (c) prepare the annual work programme and budget of the Office, implement same upon approval and present activities report.
   (d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work programme of the Office; and
   (e) represent the Office in all its dealings with third parties.
3) The Director General may delegate part of his power and duties to the employees of the Office.

12. *Budget*

1) The budget of the Office shall be drawn from the following sources:
   (a) Subsidy allocated by the Federal Government;
   (b) Income from service fees; and
   (c) Income from other sources.
2) The income of the office shall be managed according to the financial rules and regulations of the country.

13. *Books of Accounts*

1) The Office shall keep complete and accurate books of Accounts.
2) The books of accounts and financial documents of the Office shall be audited annually by the Auditor General or an auditor delegated by him.

14. *Duty to Cooperate*

Any person or governmental or private organization or institution shall have the duty to cooperate with the Office in the implemenatation of its activities.

15. *Inapplicable Laws*

Any other laws which are inconsistent with this Proclamation shall not be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

www.abyssinialaw.com



፲፮· መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

በዚህ አዋጅ፤

፩· በአዋጅ ቁጥር ፯/፲፱፻፹፯ ፣ በአዋጅ ቁጥር ፩፻፳፫/፲፱፻፹፯ እና በአዋጅ ቁጥር ፺/፲፱፻፺ ፓተንትና የመሳሰሉትን በተመለከተ ለኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን የተሰጠውን መብትና ግዴታ ፤

፪· ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያሉ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችና መመሪያዎች፤

፫· በአዋጅ ቁጥር ፩፻፸፱/፲፱፻፺፩ ኮፒራይትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ድርጅት ያለው መብትና ግዴታ፣ ለጽሕፈት ቤቱ ተላልፏል።

፲፯· የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ማመልከቻን የመቀበልና የማስተናገድ ተግባራትን የንግድ ምልክት ሕግ እስኪወጣ ድረስ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይጠቀምበት በነበረው መመሪያ መሠረት ያከናውናል።

፲፰· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

16. *Transfer of Rights and Obligations*

In this Proclamation:

1) The rights and obligations of the Ethiopian Science and Technology Commission concerning to patents and related matters under Proclamation No.7/1995, Proclamation No.123/1995 and Proclamation No.90/1997;
2) All relevant documents and directives related to trademark in the Ministry of Trade and Industry, and
3) The rights and obligations of the Ethiopian National Archives and Library related to copyright under Proclamation No. 179/1999 shall be transferred to the Office.

17. *Transitory Provisions*

The Office shall receive and process trademark applications in accordance with the directive used by the Ministry of Trade and Industry until a trademark law is enacted.

18. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of 8th day of April, 2003.

Done at Addis Ababa, this 8th day of April, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE